የመንገድ ደህንነትና መድን ፈንድ አገልግሎት
Road Safety & Insurance Fund Service

# የተሽከርካሪ ደህንነት ቀበቶ እና የህፃናት ደህንነት መጠበቂያ መሳሪያ አጠቃቀምን ለመወሰን የወጣ መመሪያ (ማሻሻያ) ቁጥር…/ 2017 ዓ.ም

**ሐምሌ/2016 ዓ.ም**

**አዲስ አበባ**

## 1. መግቢያ

የመንገድ ትራንስፖርት ለአንድ ሀገር ሁለንተናዊ እድገት የማይተካ ሚና እንዳለው የሚካድ አይደለም፡፡ ሚናውንም ደህንነቱ የተጠበቀ ለማድረግ በቴክኖሎጂ የተደገፈና በህግ ማዕቀፍ የሚመራ መሆን ይኖርበታል፡፡ ከነዚህም መንገዶች ውስጥ በማንኛውም እንቅስቃሴ የደህንነት መጠበቂያ መሳሪያዎችን መጠቀም ወሳኝ ነው፡፡ የአለም የጤና ድርጅት እንዳወጣው መረጃ በህዝብ ትራንስፖርት አማካኝነት የሚንቀሳቀሱ አካላት በጉዞ ወቅት የደህንነት ቀበቶ በአግባቡ ቢጠቀሙ አደጋ በሚያጋጥማቸው ወቅት አሽከርካሪውንና ከፊት የሚቀመጡ አካላት ከ45% እስከ 50% ለሞት ተጋላጭነታቸውን እንደሚቀንስና ከኋላ የሚቀመጡ ተጓዦችን ደግሞ ከ25% እስከ 35% ከሞት ሊታደጋቸው እንደሚችል ያሳያል፡፡ በሃገራችንም በደህንነት ቀበቶ አለመጠቀም ምክንያት የደረሱ አደጋዎች ጥናት ተደርጎባቸው የተቀመጡ ባይሆንም ለአደጋዎቹ አስከፊነት የደህንነት ቀበቶን አለመጠቀም ከፍተኛ ድርሻ እንዳለው የማይካድ ነው፡፡

በአጠቃላይ የደህንነት ቀበቶ ማሰር እና እድሜያቸው ከ7 ዓመት በታች የሆኑ ህፃናት በተሽከርካሪ ውስጥ ሆነው በሚጓዙበት ጊዜ የህፃናት ደህንነት ማቀፊያ መሳሪያ የሚጠቀሙ ከሆነ አሽከርካሪው ወይም ተሳፋሪው አደጋዎች በሚከሰቱበት ወቅት በፊተኛው ወይም በጎን ባሉ የተሽከርካሪው መስታወቶች ተስፈንጥረው እንዳይወጡና በዚህ ምክንያት ይደርስ የነበረውን ከፍተኛ አደጋ ለመቀነስ ከማስቻሉም በላይ አሽከርካሪዎች በአደጋ ወቅት ተሽከርካሪውን ለመቆጣጠር እንዲችሉ ያግዛል በተጨማሪም አደጋ በሚከሰትበት ወቅት አሽከርካሪውና ተሳፋሪዎች ተሽከርካሪው ውስጥ ወይም ከተሽከርካሪው ውጪ ካሉ ግዑዝ ነገሮች ጋር ከመጋጨት እንደሚታደግ ይታመናል፡፡

በመሆኑም በመንገድ ትራንስፖርት ትራፊክን ለመቆጣጠር የወጣ የሚኒስትሮች ም/ቤት ደንብ ቁጥር 557/2016 በአንቀፅ 7 እና 50 ስር እንደተደነገገው ማንኛውም አሽከርካሪ ከሞተር ብስክሌት በቀር የደህንነት ቀበቶ ሳያስር ወይም በተሽከርካሪው የፊት እና የኋላ መቀመጫዎች የተሳፈሩ ሰዎች በሙሉ የደህንነት ቀበቶ ማሰራቸውን እንዲሁም ከ7 ዓመት በታች የሆኑ ህፃናትን በተሽከርካሪ ውስጥ ይዞ ሲንቀሳቀስ በተሽከርካሪው የኋለኛው ክፍል ባለው መቀመጫ በህፃናት ደህንነት መጠበቂያ መሳሪያ መታሰራቸውን ሳያረጋግጥ በመንገድ ላይ ማንኛውንም ተሽከርካሪ ማሽከርከር እንደሌለበት በሚደነግገው መሰረት **ሚኒስቴሩ** ይህን የማስፈፀሚያ መመሪያ/ማሻሻያ/ አውጥቷል፡፡

## ክፍል አንድ

# ጠቅላላ ድንጋጌ

## 1. አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ የተሽከርካሪ ደህንነት ቀበቶ እና የህፃናት ደህንነት መጠበቂያ መሳሪያ አጠቃቀምን ለመወሰን የወጣ መመሪያ (ማሻሻያ) ቁጥር.../ 2017 ዓ.ም ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

## 2. ትርጓሜ

በመመሪያው ውስጥ የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ፡-

1. **‹‹ደንብ››** ማለት የመንገድ ትራንስፖርት ትራፊክ መቆጣጠሪያ ደንብ ቁጥር 557/**2016** ነው፡፡
2. **‹‹ሚኒስቴር››** ማለት የትራንስፖርትና ሎጀስቲክስ ሚኒስቴር ማለት ነው
3. **‹‹አገልግሎት››**ማለት የመንገድ ደህንነትና መድን ፈንድ አገልግሎት ማለት ነው፡፡
4. **‹‹የትራንስፖርት ቢሮ››** ማለት ትራንስፖርትን ለመምራት ስልጣን የተሰጠው የክልል ወይም የከተማ አስተዳደር ትራንስፖርትን የሚመራ አካል ነው፡፡
5. **‹‹የሚመለከተው አካል››** ማለት የደህንነት ቀበቶ በተሽከርካሪው ላይ እንዲኖር ለመፍቀድ በህግ ስልጣን የተሰጠው ወይም ውክልና ያለው አካል ነው፡፡
6. **‹‹የደህንነት ቀበቶ›› ማለት** በተሽከርካሪ ወንበሮች ላይ የተገጠመ ቀበቶ ሆኖ የአሽከርካሪውንና የተሳፋሪዎችን ወገብ እና/ወይም ትከሻ ከተሽከርካሪው ወንበር ጋር በማቆራኘት በአደጋ ጊዜ አሽከርካሪው ወይም ተሳፋሪው ለጉዳት በቀላሉ እንዳይጋለጥ የሚረዳ ቀበቶ ነው፡፡
7. **‹‹የህፃናት ደህንነት መጠበቂያ መሳሪያ››** ማለት በተሽከርካሪ ወንበሮች ላይ ሆኖ ከ7 ዓመት በታች የሆኑ ህፃናት በተሽከርካሪ ውስጥ ሆነው በሚጓዙበት ጊዜ እንዳይንቀሳቀሱ አቅፎ ወይም አስሮ በመያዝ በአደጋ ጊዜ ለጉዳት በቀላሉ እንዳይጋለጡ የሚያግዝ መሳሪያ ነው፡፡
8. ***ተቀጣይ የህፃናት ቀበቶ፡- ማለት ከአውቶሞቢል ውጭ በሚሳፈሩ ከሰባት አመት በታች የሆኑ ማንኛውም ህፃናት አብሯቸው ከሚጓዙ አካላት ቀበቶ ላይ ተቀጥሎ ህፃናትን የሚያስር የደህንነት መጠበቂያ ቀበቶ አይነት ነው፡፡***

### 3. የተፈፃሚነት ወሰን

ይህ መመሪያ በኢትዮጵያ መንገዶች ውስጥ በሚንቀሳቀሱ በሁሉም ተሽከርካሪዎች ላይ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

## 4. የመመሪያው ዓላማ

የዚህ መመሪያ ዓላማ በተሽከርካሪዎች ላይ የደህንነት ቀበቶ እና የህፃናት ደህንነት መጠበቂያ መሳሪያ እንዲጠቀሙ በማድረግ በአሽከርካሪዎችና በተሳፋሪዎች ላይ በአደጋ ወቅት የሚደርሰውን የመንገድ ትራፊክ ግጭት አስከፊነት መቀነስ ነው፡፡

# ክፍል ሁለት

## የተሽከርካሪ ደህንነት ቀበቶ እና የህፃናት ደህንነት መጠበቂያ መሳሪያ የሚገጠምላቸው ተሽከርካሪዎች

**5. የደህንነት ቀበቶ ስለማሰር**

1. ማንኛውም ተሽከርካሪ የኢትዮጵያን የጥራት ደረጃ የጠበቀ የደህንነት ቀበቶ ሳይገጠምለት ተሳፋሪን ጭኖ ከቦታ ቦታ መንቀሳቀስ የለበትም፡፡
2. ማንኛውም ተሳፋሪ ተሽከርካሪው በእንቅስቃሴ ላይ በሚሆንበት ጊዜ የደህንነት ቀበቶ ማሰር አለበት፡፡
3. ማንኛውም አሽከርካሪ ከሞተር ብስክሌት በስተቀር ተሽከርካሪውን በሚያሽከረክርበት ወቅት በተሽከርካሪው የፊት እና የኋላ መቀመጫዎች የተሳፈሩ ተሳፋሪዎች በሙሉ የደህንነት ቀበቶ ማሰራቸውን ማረጋገጥ አለበት፡፡
4. ማንኛውም በሀገር አቋራጭ የህዝብ ማመላለሻ ትራንስፖርት ስራ ላይ የተሰማራ አሽከርካሪ ህፃናት ይዘው ለሚጓዙ ተሳፋሪዎች ከተሳፋሪው ቀበቶ ላይ ተቀጥሎ የታቀፈውን ህፃን የሚያስር ተቀጣይ ቀበቶ መጠቀም አለበት፡፡
5. የዚህ አንቀጽ ንዑስ ቁጥር 1 ድንጋጌ ቢኖርም የመጫን አቅማቸው ከ 24 ሰው በላይ የሆኑ የከተማ የብዙሃን ትራንስፖርት አገልግሎት የሚሰጡ ተሽከርካሪዎች ከአሽከርካሪው እና ከተሽከርካሪው የፊት መቀመጫ ከሚቀመጡ ተሳፋሪዎች በስተቀር ሌሎች ተሳፋሪዎች የደህንነት ቀበቶ እንዲያስሩ አይገደዱም፡፡
6. በአስመጪዎች ወደ ሀገር ውስጥ የሚገቡ አዲስ ተሽከርካሪዎች የኢትዮጵያን የጥራት ደረጃ የሚያሟላ የደህንነት ቀበቶ ለአሽከርካሪውና ለተሳፋሪዎች የተገጠመላቸው መሆን አለባቸው፡፡

**6.** የህፃናት የደህንነት መጠበቂያ መሳሪያ ስለመጠቀም

1. ማንኛውም ከ7 ዓመት በታች የሆኑ ህፃናትን አሳፍሮ የሚጓዙ የግል አውቶሞቢል ተሽከርካሪዎች በሚጓዙበት ጊዜ  ህፃናቱ እንዳይንቀሳቀሱ አቅፎ ወይም አስሮ የሚይዝ የኢትዮጵያን የጥራት ደረጃ የጠበቀ የደህንነት መጠበቂያ መሳሪያ መጠቀም አለባቸው፡፡
2. ማንኛውም ዕድሜያቸው ከ 1 ዓመት በታች ወይም ከ10 ኪ.ግ በታች ወይም ከ105 ሴ.ሜ በታች የሆኑ ጨቅላ ህፃናትን አሳፍሮ የሚጓዙ አሽከርካሪዎች መጠቀም ያለባቸው የህፃናት ደህንነት መጠበቂያ ከተሽከርካሪው የኋለኛው ክፍል  ጨቅላ ህፃኑን በጀርባ አንጋሎ በሚያስተኛው የደህንነት መጠበቂያ መሳሪያ መጠቀም አለባቸው፡፡
3. ማንኛውም ዕድሜያቸው ከ 1 እስከ 4 ዓመት ወይም ከ9 እስከ 18 ኪ.ግ ወይም ከ100 እስከ 135 ሴ.ሜ የሆኑ ታዳጊ ህፃናትን አሳፍሮ የሚጓዙ አሽከርካሪዎች ከጀርባው ቀና ያለ የህፃናት ደህንነት መጠበቂያ ከተሽከርካሪው የኋለኛው ክፍል  መጠቀም አለባቸው፡፡
4. ማንኛውም ዕድሜያቸው ከ 4 እስከ 7 ዓመት ወይም ከ15 እስከ 25 ኪ.ግ ወይም ከ125 ሴ.ሜ በላይ የሆኑ ልጆቹን አሳፍሮ የሚጓዙ አሽከርካሪዎች ከወንበሩ ከፍ አድርጎ የሚያስቀምጥ የልጆች ደህንነት መጠበቂያ ከተሽከርካሪው የኋለኛው ክፍል  መጠቀም አለባቸው፡፡

**7.** ልዩ ሁኔታ

1. በጤና ዕክል ምክንያት የደህንነት መጠበቂያ ቀበቶ መጠቀም የማይችሉ አሽከርካሪዎች ወይም ተሳፋሪዎች ይህንኑ ሊያረጋግጥ የሚችል የህክምና ማስረጃ ማቅረብ አለባቸው፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የሚቀርበው የህክምና ማስረጃ ከሆስፒታል በሀኪሞች ቦርድ የተረጋገጠ መሆን ይኖርበታል፡፡
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 መሰረት የሚቀርበው የህክምና ማስረጃ በየዓመቱ መታደስ አለበት፡፡
4. የዚህ መመሪያ ድንጋጌ በባለሁለት እና ባለሶስት እግር ተሽከርካሪ አሽከርካሪዎች ላይ ተፈጻሚ አይሆንም፡፡

# ክፍል ሶስት

## የተለያዩ አካላት ተግባርና ኃላፊነት

## 8. የትራንስፖርትና ሎጀስቲክስ ሚኒስቴር ተግባርና ኃላፊነት

1. የተሽከርካሪ የደህንነት ቀበቶ እና የህፃናት ደህንነት መጠበቂያ መሳሪያ መመሪያን ማጽደቅና አተገባበሩን መከታተል፡፡
2. ማንኛውም ተሽከርካሪ የደህንነት ቀበቶ እና የህፃናት ደህንነት መጠበቂያ መሳሪያ በወጣው የኢትዮጵያ የጥራት ደረጃ መሰረት ሳይገጥም ወደ አገር ውስጥ እንዳይገባ የመከልከል፤
3. ማንኛውም የደህንነት ቀበቶ እና የህፃናት ደህንነት መጠበቂያ መሳሪያ ወደ ሀገር ውስጥ ሲገባ የኢትዮጵያ የጥራት ደረጃ የጠበቀ መሆኑን የመከታተል፤
4. ተሽከርካሪዎች የትራንስፖርት አገልግሎት ለውጥ በሚያደርጉበት ወቅት የኢትዮጵያ የጥራት ደረጃን የጠበቀ የአሽከርካሪ እና የተሳፋሪ ቀበቶ ማካተቱን የማረጋገጥ፤
5. የኦፕሬተር ፍቃድ የሚሰጣቸው ሀገር አቋራጭ የህዝብ ማመላለሻ ተሽከርካሪዎች ለሁሉም መንገደኞች የደህንነት ቀበቶ እና ተቀጣይ የህፃናት ቀበቶ እንዲገጥሙ ይቆጣጠራል፣ ይከታተላል፡፡

### 2. የአገልግሎቱ ተግባርና ኃላፊነት

1. በሃገሪቱ የሚገኙ የተሽከርካሪ አይነትን እና መጠንን ያማከለ የደህንነት ቀበቶ እና የህፃናት ደህንነት መጠበቂያ መሳሪያ ዲዛይን ከኢትዮጵያ ስታንዳርድ ኢኒስቲቲዩት ጋር በመቀናጀት መስፈርት እንዲወጣ ያደርጋል፣ያሻሽላል፣ ተግባራዊነቱን ይከታተላል፡፡
2. አገልግሎቱ የደህንነት ቀበቶ አጠቃቀም እና የህፃናት ደህንነት መጠበቂያ መሳሪያ ስርዓትን ለሚመለከታቸው አካላት ያስተዋውቃል፡፡
3. አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ አገልግሎቱ የደህንነት ቀበቶ አጠቃቀም እና የህፃናት ደህንነት መጠበቂያ መሳሪያ የሚተገበርበትን ጊዜ፣ የተሽከርካሪ እና የመቀመጫ ዓይነት የቅደም-ተከተል መርሐ-ግብር በማውጣት ተግባራዊ እንዲሆኑ ያደርጋል፡፡

4. በጉምሩክ በኩል ወደሃገር የሚገቡ ተሽከርካሪዎች በሁሉም ወንበሮች ላይ በአምራች ፋብሪካው ወይም አገልግሎቱ በኢትዮጲያ ባለው (Standard) መሰረት የደህንነት ቀበቶ ያላቸው ስለመሆኑ ቁጥጥር ያደርጋል፡፡
5. የተሽከርካሪ ምርመራ ተቋማት ለተሽከርካሪዎች የቴክኒክ ምርመራ ሲያደርጉ የደህንነት ቀበቶ እና የህፃናት ደህንነት መጠበቂያ መሳሪያ መስራቱን በአግባቡ እያረጋገጡ ስለመሆናቸው ክትትል ድጋፍና ቁጥጥር ያደርጋል፡፡
6. አገልግሎቱ በተሽከርካሪዎች ላይ የተገጠመው የደህንነት ቀበቶ እና የህፃናት ደህንነት መጠበቂያ መሳሪያ በወጣለት መስፈርት መሰረት መሆኑን እና በተገቢው አጠቃቀም መፈጸሙን ይቆጣጠራል፡፡
7. የደህንነት ቀበቶ እና የህፃናት ደህንነት መጠበቂያ መሳሪያ አተገባበር ቁጥጥርን በተመለከተ አገልግሎቱ በህግ በተሰጠው ስልጣን መሰረት እንደአስፈላጊነቱ በውክልና ወይንም በቅንጅት የሚከናወንበትን መንገድ ይነድፋል፡፡
8. በሁሉም የሃገሪቱ ክፍል የደህንነት ቀበቶ እና የህፃናት ደህንነት መጠበቂያ መሳሪያ አተገባበር ወጥነት ባለው መልኩ እየተከናወነ መሆኑን ይከታተላል፤ ለአፈጻጸሙ መሳካትም ድጋፍ ያደርጋል፡፡
9. የኢትዮጵያን የጥራት ደረጃ ምልክት የሌለው ወይም በተሽከርካሪ አምራች ፋብሪካው ያልተገጠመ የደህንነት ቀበቶ እና የህፃናት ደህንነት መጠበቂያ መሳሪያ በቁጥጥር ወቅት ሲገኝ ዕርምጃ ይወስዳል፡፡

**3. የትራንስፖርት ቢሮ ሃላፊነት**

1. ይህንን መመሪያ መሰረት በማድረግ በሚወጣው የጊዜ ሰሌዳ መሰረት ነባር ተሽከርካሪዎች በሚወጣው መስፈርት ለሁሉም ወንበሮች የደህንነት ቀበቶ እና የህፃናት ደህንነት መጠበቂያ መሳሪያ ስለ መግጠማቸው ይከታተላል፤ ያረጋግጣል፣ይቆጣጠራል፡፡
2. በትራንስፖርት ቢሮ የኦፕሬተር ፍቃድ የሚሰጣቸው የመካከለኛ እና አነስተኛ የህዝብ ማመላለሻ ተሽከርካሪዎች ለሁሉም መንገደኞች የደህንነት ቀበቶ እና ተቀጣይ የህፃናት ቀበቶ እንዲገጥሙ ይቆጣጠራል፣ ይከታተላል፡፡
3. የደህንነት ቀበቶ እና የህፃናት ደህንነት መጠበቂያ መሳሪያ አተገባበርን በተመለከተ የቁጥጥር ተግባራትን ያከናውናል፡፡
4. የትራንስፖርት ቢሮዎች በደህንነት ቀበቶ እና የህፃናት ደህንነት መጠበቂያ መሳሪያ መመሪያ አተገባበር እና አፈጻጸም ዙርያ ለሚመለከታቸው አካላት የግንዛቤ ማስጨበጫ ስራ ይሰራል፡፡
5. ተሽከርካሪዎች አመታዊ የቴክኒክ ምርመራ ሲያደርጉ በአምራች ድርጅቱ በተገጠመላቸው ወንበር ልክ ፋብሪካው ወይም አገልግሎቱ ባወጣው ዲዛይን እና ደረጃ የደህንነት ቀበቶ እና የህፃናት ደህንነት መጠበቂያ መሳሪያ የተገጠመላቸው መሆኑን ያረጋግጣል፡፡

6. የተሽከርካሪ ምርመራ ተቋማት ለተሽከርካሪዎች የቴክኒክ ምርመራ ሲያደርጉ የደህንነት ቀበቶ እና የህፃናት ደህንነት መጠበቂያ መሳሪያ በትክክል ስለ መስራቱ ማረጋገጣቸውን ይቆጣጠራል፡፡
7. የኢትዮጵያን የጥራት ደረጃ ምልክት የሌለው የደህንነት ቀበቶ እና የህፃናት ደህንነት መጠበቂያ መሳሪያ በቁጥጥር ወቅት ሲገኝ የሚወሰደው ህጋም ዕርምጃ እንደተጠበቀ ሆኖ ባለንብረቱ አሟልቶ እስኪያመጣ የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፍቃዱን ይዞ ይቆያል፡፡

## 4. የትራፊክ ተቆጣጣሪ ተግባርና ኃላፊነት

1. የደህንነት ቀበቶ እና የህፃናት ደህንነት መጠበቂያ መሳሪያ አተገባበርን በተመለከተ ቁጥጥር የማድረግና እርምጃ የመውሰድ፤
2. የኢትዮጵያን የጥራት ደረጃ ምልክት የሌለው ወይም በተሽከርካሪ አምራች ፋብሪካው ያልተገጠመ የደህንነት ቀበቶ እና የህፃናት ደህንነት መጠበቂያ መሳሪያ በቁጥጥር ወቅት ሲገኝ የሚወሰደው ህጋም ዕርምጃ እንደተጠበቀ ሆኖ ባለንብረቱ አሟልቶ እስኪያመጣ የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፍቃዱን ይዞ ይቆያል፡፡

## 5. የተሽከርካሪው ባለቤት ኃላፊነት

1. የነባር ወይም የአዲስ ተሽከርካሪ ባለንብረት አገልግሎቱ ባወጣው ስታንዳርድ መሰረት የደህንነት ቀበቶ እና የህፃናት ደህንነት መጠበቂያ መሳሪያ በተሽከርካሪው ላይ የማሟላት፤
2. የደህንነት ቀበቶው እና የህፃናት ደህንነት መጠበቂያ መሳሪያ በተገቢው ሁኔታ የሚሰራ መሆኑን በየጊዜው የማረጋገጥ፤

## 6. የአሽከርካሪው ኃላፊነት

1. አሽከርካሪው የደህንነት ቀበቶውን በአግባቡ ማድረግና ተሳፋሪዎችም በአግባቡ ማድረጋቸውን ማረጋገጥ አለበት፤
2. አሽከርካሪው የሚያሽከረክረው ተሽከርካሪ የኢትዮጵያን የጥራት ደረጃ የጠበቀ የደህንነት ቀበቶ እና የህፃናት ደህንነት መጠበቂያ መሳሪያ ያሟላ መሆኑን ማረጋገጥ፡፡
3. የደህንነት ቀበቶውን እና የህፃናት ደህንነት መጠበቂያ መሳሪያ ንጽህናና ደህንነትን መጠበቅ፤

## 7. የተሳፋሪው ሀላፊነት

1. ማንኛውም ተቀምጦ የሚሄድ ተሳፋሪ በሚሳፈረው ተሽከርካሪ ላይ የደህንነት ቀበቶ በአግባቡ የማሰር፡፡
2. የደህንነት ቀበቶውን የሚጎዳ ማንኛውም አይነት ድርጊት ያለመፈጸም፣

## 8. የተሽከርካሪ ምርመራ ተቋማት ኃላፊነት

ማንኛውም የተሽከርካሪ ምርመራ ተቋም፡-

በዓመታዊ የቴክኒክ ምርመራ ወቅት የአሽከርካሪውና የተሳፋሪዎች የደህንነት ቀበቶ እና የህፃናት ደህንነት መጠበቂያ መሳሪያ ስለመኖሩ እና በስታንዳርዱ መሰረት ስለመገጠሙ ማረጋገጥ፡፡

## 9. ተፈፃሚነት የማይኖራቸው ህጎች

የዚህን መመሪያ ድንጋጌ የሚቃረን ማንኛውም መመሪያ ወይም ልማዳዊ አሰራር ተፈፃሚነት አይኖረውም፡፡

**10. የተሻሩ መመሪያዎች**

የተሽከርካሪ የደህንነት ቀበቶ በተሽከርካሪው ወንበሮች ላይ እንዲኖርና ተግባራዊ እንዲደረግ የወጣ መመሪያ ቁጥር 694/2013 በዚህ መመሪያ ተሽሯል፡፡

**11. መመሪያውን ስለማሻሻል**

አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ሚኒስቴሩ ይህን መመሪያ ሊያሻሽል ይችላል፡፡

**12. ቅጣት**

አሽከርካሪው የደህንነት ቀበቶ ሳያደረግ እና ተሳፋሪዎች ማድረጋቸውን ሳያረጋግጥ እንዲሁም የህፃናት ደህንነት መጠበቂያ መሳሪያ መኖሩን ሳያረጋግጥ ህፃናትን አሳፍሮ ያሽከረከር በመንገድ ትራንስፖርት ትራፊክ መቆጣጠሪያ ደንብ ቁጥር557/2016 መሰረት ይቀጣል፡፡

**13. መመሪያዉ የሚጸናበት ጊዜ**

ይህ መመሪያ ከ---------- ቀን------------2017ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

ዶ/ር ዓለሙ ስሜ

የትራንስፖርትና ሎጀስቲክስ ሚኒስቴር ሚኒስትር